# በሌላ አገር ባለስልጣን የተደረገ ፊርማ ሃቀኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ (Apostille Authentication) የምስክር ወረቀት

አፖስቲል (Apostille) ዶኩመንት ሃቀኛ መሆኑን ማረጋገጥ ምን ማለት ነው?

በሌላ አገር ጥቅም ላይ የሚውል በአንድ ዶኩመንት ላይ የተደረገ የባለስልጣን ፊርማ ሃቀኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት። ይህ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ያረጋግጣል።

- ዶኩመንቱን የፈረመው ባለስልጣን ሃቀኛ መሆኑን ያረጋግጣል
- ይህ ፈራሚ ባለስልጣን በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ዶኩመንቱ ላይ ለመፈረም የበቃው
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤ በዶኩመንቱ ላይ የሰፈረው ማህተም ሃቀኛ መሆኑን ያረጋግጣል። ለምሳሌ ባለስልጣኑ የተጠቀመበት ማህተም።

## አፖስቲል ወይም እንዲህ ዓይነቱ የሃቀኝነት ማረጋገጫ እንዴት እንደሚገኝ

በሚነሶታ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ማረጋገጫ ማግኘት የሚቻለው በሁለት ዓይነት መንገዶች ነው፡

### በአካል በመገኘት (ቀጠሮ በማድረግ)

በባለስልጣን ፊርማ የተሸኘውን ወይም ኦሪጂናል ዶኩመንቱን በቀጠሮው ቀን ይዞ በአካል መምጣት። ማስታወሻ፡ የባለዶኩመንቱን ማንነት የማረጋገጥ አገልግሎት የለንም።

በኦንላይን ወደ ማይክሮሶፍት ቡኪንግስ (Microsoft Bookings ) በመግባት ቀጠሮ መውሰድ ይችላሉ። ማስታወሻ፡ ቀጠሮ የሚወሰደው ከቀጠሮው ቀን አስራ አራት ቀናት በፊት ነው።

ዋጋዎችና ተቀባይነት ያለው አከፋፈል፡

- ለእያንዳንዱ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስርያ ቤቱ $5.00 ያስከፍላል።
- ተቀባይነት ያላቸው አከፋፈሎች፤ የብድር ካርድ (Credit card)፣ የዴቤት ካርድ ( debit card)፣ ጥሬ ገንዘብ፤ ቼክ (check) ወይም የገንዘብ ትእዛዝ (money order)።

ቀጠሮ የሚደረግበት ቦታ:

Minnesota Secretary of State
First National Bank Building
332 Minnesota Street, Suite N201
Saint Paul, MN 55101

### በፖስታ

ጥያቄዎን በጽሁፍ (በፖስታ) ለማቅረብ ከፈለጉ፤ በባለስልጣን የተፈረመውን ዶኩመንቶን፣ ወይም ኦሪጂናል ዶኩመንቶን እንዲሁም የሚከፈለውን ክፍያና የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጦት በመጠየቅ የሞሉትን ፎርም (Authentication Request Form) አያይዘው ይላኩ።

ደብዳቤዎ ወደ ሌላ የተለየ አድራሻ እንዲላክሎ የተለየ መመርያ ካልሰጡ ወይም የተከፈለ ቴምብር ያለበት ፖስታ ካልላኩ በስተቀረ፤ የምስክር ወረቀት እንዲሰጦት በመጠየቅ በሞሉት ፎርም (Authentication Request Form) ላይ ወደ ተጻፈው አድራሻ መላክ አለቦት።

**አስተውሉ:** የላኩት ደብዳቤ የት እንደደረሰ ለመከታተል የፖስታ ክትትል አገልግሎት ለመጠቀም ከፈለጉ፣ አስቀድሞ የተከፈለ ፌዴክስ (FedEx)፣ ዩ-ኤስ-ፒ-ኤስ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ደብዳቤዎች (USPS Priority Mail) ወይም ዩ-ፒ-ኤስ (UPS) መለያ ያለበት መጠቀም አለቦት። ይህንን ካልፈለጉ ግን መስርያ ቤታችን ዶኩሜንቶችዎን በመደበኛው የዩ-ኤስ የፖስታ አገልግሎት (UPS) ካለምንም ክፍያና ካለ የፖስታ መከታተል አገልግሎት ይልካል።

ዋጋዎችና ተቀባይነት ያለው አከፋፈል:

- ለእያንዳንዱ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤ መስርያ ቤቱ $5.00 ያስከፍላል።
- ተቀባይነት ያላቸው አከፋፈሎች፤ ለሚኖሶታ የአገር ውስጥ ሚኒስቴር የተጻፈ ቼክ (check) ወይም የገንዘብ ትእዛዝ (money order)።

የፖስታ አድራሻ:

Minnesota Secretary of State
First National Bank Building
332 Minnesota Street, Suite N201
Saint Paul, MN 55101

## የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መመርያ

***የተመሰከረላቸው ኦሪጂናል ዶኩመንቶች*** ሌላ ማረጋገጫ አያስፈልጋቸውም። እነኚህ ዓይነት ዶኩመንቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- **የልደት የምስክር ወረቀት እና የሞት የምስክር ወረቀት በሚኖሶታ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይረጋገጣሉ።** ከሚኖሶታ የልደት ወይም የሞት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፤ በሚኖሶታ የጤና ጥበቃ መምሪያ ውስጥ ከሚገኘው የአስቸኳይ ኩነት መዝገብ ክፍል (**The Office of Vital Records at the Minnesota Department of Health**) ጋር ይገናኙ፤ የመገናኛውን ዘዴ (link) ለማግኘትም ኮንትሮል+ክሊክ (Control+Link) ይጫኑ።

- **በሚኖሶታ ካውንቲ (አውራጃ) የተሰጡ የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች ወይም የመንጃ ፈቃዶች:** የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች፤ የጋብቻው የምስክር ወረቀት በተሰጠበት በአውራጃው መዝገብ ቤት ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። ከሚኖሶታ የተረጋገጠ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ቅጂ ለማግኘት ከፈለጉ፤ የጋብቻው የምስክር ወረቀት በተሰጠበት አውራጃ መጠየቅ ይችላሉ ወይም ኦንላይን ገብተው የጋብቻ የምስክር ወረቀት **Marriage Certificates** የሚለውን ኮንትሮል+ክሊክ (Control+Link) የሚለውን በመጫን ይጎብኙ።

- **የተረጋገጡ የፍቺ መግለጫዎችና የተሰጡ ፍርዶች ቅጂ:** እነኚህን ቅጂዎች፤ የፍችው ፍርድ በተሰጠበት አውራጃ ማግኘት ይቻላል። እነኚህ የተመሰከረላቸው ቅጂዎች እዚህ **here** ይገኛሉ።

- **የተመሰከረላቸውና የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች ዶኩመንት ቅጂዎች፤** በሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ በንግድ ስራ ድርጅት መዝገብ ቤት ማግኘት ይቻላል። እነኚህ የተመሰከረላቸው ቅጂዎች እዚህ **here** ይገኛሉ።

***ከሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) አስፈላጊው ማረጋገጫ ማግኘት የሚገባቸው ዶኩመንቶች፤*** እንደዚህ ዓይነቶችን ዶኩመንቶች ያጠቃልላሉ:

- **የግል ዶኩመንቶች (ለምሳሌ የሌላ ሰው ልጅን ለማሳደግ የሚሰጡ የፈቃድ ወረቀቶች፤ በመሃላ የተሰጡ መግለጫዎች፣ የውክልና ወረቀቶች...ወዘተ)**

የግል ዶኩመንቶች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) መረጋገጥ አለባቸው።

- **እንዲሁም ከሚኖሶታ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከልጆች መዋያ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ካሉ ትምህርት ቤቶች የተሰጡ የትምህርት የምስክር ወረቀቶች**

በትምህርት ቤት ባለስልጣን የተፈረሙ ወይም በትምህርት ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ማህተም የተደረገባቸው የትምህርት የምስክር ወረቀቶች ተቀባይነት የላቸውም። የትምህርት የምስክር ወረቀቶች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) የተረጋገጡ መሆን አለባቸው።

**አስተውሉ፡** በትምህርት ቤት የመዝገብ ክፍል በታሸገ ፖስታ ለሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ጸሃፊ የተላኩ የትምህርት ምስክር ወረቀቶች፤ በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) የተመሰከሩ መሆናቸውን ለማየት የታሸገውን ፖስታ የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ባለስልጣን ሊከፍተው ይገባል።

- **ከሚኖሶታ ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ ወይም ከህጻናት መዋያ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የሚሰጡ ዲፕሎማዎች**

በትምህርት ቤት ባለስልጣን የተፈረሙና በትምህርት ቤቱ መዝገብ ቤት ሹም ማህተም የተደረገባቸው የትምህርት ዲፕሎማዎች ተቀባይነት የላቸውም። ዲፕሎማዎች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) የታዩና የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆን የ አለባቸው።

**አስተውሉ፡** ዲፕሎማዎን ለመስጠት የፈልጉት አገር የዲፕሎማዎን ቅጂ ነው የሚፈልገው ወይስ ዋናውን ኦሪጂናል ዲፖሎማ መሆኑንና አለመሆኑን በቅድሚያ ያረጋግጡ። ዋናው ኦሪጂናል ወይም ቅጂ በመጀመርያ በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) በተገቢው መንገድ መረጋገጥ አለበት።

***ሃቅነታቸው በደንብ የተረጋገጠ ዶኩመንቶች ተቀባይነት የማያገኙበትን ዕድል ለመቀነስ፤ ትክክለኛውንና ተገቢውን እውቅና ለማግኘት የሚከተሉት መሟላት ያስፈልጋል፡***

- ***ተገቢ ማረጋገጫ*** ፡ በሚኖሶታ የህግ ቁጥር 358.65 ([link]) መሰረት በዚህ መገናኛ ለመግባት ይጫኑ። ይህ የሚሰጠው የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆን አለበት፤ ከኦሪጂናሉ ዶኩመንት ጋር አብሮ ወይም ተያይዞ መቅረብ አለበት። የሚከተሉትንም ማከል አለበት፡
  - የተሰጠው የሃቅነት ማረጋገጫ የት ቦታ እንደተሰጠ (ለምሳሌ ራምሲ ካውንቲ፤ የሚኖሶታ ክፍለሃገር..) ማመልከት አለበት።
  - ሃቀኛነትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ ነገሮች ያለበት መሆን አለበት (ለምሳሌ ሲፈረም ያየ፣ እውነተኛና ትክክለኛ ቅጂ መሆኑን የሚያመለክት መግለጫ የያዘ፤ በመሃላ የተሸኘ...ወዘተ)
  - ሃቀኛነትን ያረጋገጠው ባለስልጣን ሹመት ወይም ስልጣን ( ለምሳሌ የሃቀኛነት መስካሪ ባለስልጣን( Notary Public) መሆኑ የተጻፈበት መሆን አለበት።
  - የዶኩመንቱ ሃቀኛነት የተረጋገጠበት ቀን
  - የሃቀኛነት ምስክር ሰጪ ባለስልጣን ፊርማ
  - የሃቀኛነት ምስክር ሰጪ ባለስልጣን ማህተም

  የሃቀኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (*Certificate of Notarial Act (notarization)*) ህጎች ከወደታች ይገኛሉ።

  - የፊርማ ማመሳከሪያ ፒ-ዲ-ኤፍ [Attestation of a Signature (PDF)]
  - የዶኩመንት ማመሳከሪያ [Attestation of a Document (PDF)]
  - የግለሰብ ዓቅም/ችሎታ እውቅና [Acknowledgment in Individual Capacity (PDF)]
  - የግለሰብ የውክልና ብቁነት [Acknowledgment in Representative Capacity (PDF)]
  - በመሃላ የተሰጠ ማረጋገጫ [Verification Upon Oath (PDF)]

- ***የሚኖሶታ ትክክለኛ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን ኮሚሽን ማህተም፡*** *ይህ የዶኩመንት ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ ባለስልጣን ዶኩመንቶ ሃቀኛ ዶኩመንት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን የሚያሟላ መሆን አለበት፡:*
    - ይህ ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ ባለስልጣን፤ እውቅናውን ወይም ማረጋገጫውን በሚሰጥበት ግዜ፤  በስራ ላይ ያለ መሆን አለበት።
    - በማህተሙ ላይ ያለው ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ ባለስልጣን ስም በኮሚሽኑ ውስጥ ካለው ስም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት።
    - በማህተሙ ላይ የሚገኘው ማህተሙ የሚቃጠልበት ቀንና በባለሰልጣኑ የተጻፈው ቀን አንድ ዓይነት መሆን አለባቸው። *ልዩነት (Exception)፡* ምንም እንኳን የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣኑ((Notary)  ለሚቀጥሉት ተጨማሪ አምስት ዓመታት የሚቆይ የስራ ፈቃዱን በስኬታማነት ቢያሳድስም፤ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን ማህተም የሚቆይበት ግዜ እስኪቃጠል ድረስ፤ ጥቅም ላይ መዋሉን መቀጠል ይችላል።

ይህ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary) በስራ ላይ እንዳለና ስሙንና የስልጣኑ ግዜ መቼ እንደሚቃጠል ለማወቅ የባለስልጣኑ መረጃ **notary database.** የሚለውን ኮንትሮል+ሊንክ በመጫን ሊያገኙት ይችላሉ። እርግጠኛ ካልሆኑ በ **apostille.oss@state.mn.us** ውስጥ በመግባት ከእኛ ጋር ተገናኙ።

**እባክዎን ያስተውሉ፡ ይህ ሃቀኛነታቸው እንዲረጋገጥ ብቁ የሆኑ ዶኩመንቶች የተሟላ ዝርዝር አይደለም፡**

## ትክክለኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) በተመለከተ ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### <u>አጠቃላይ መረጃ</u>

**ጥያቄ: ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) ሲባል ምን ማለት ነው?  ዓላማውስ ምንድነው?**

**መልስ፡** ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) ማለት በሌላ አገር ጥቅም ላይ በሚውል ዶኩመንት ውስጥ የፈረመ ባለስልጣን ፊርማ የሃቀኛ ባለስልጣን ፊርማ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማለት ነው። ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) የሚከተሉትን ያረጋግጣል፡

- በዶኩመንቱ ውስጥ የፈረመው ባለስልጣን ፊርማ ሃቀኛነት
- ይህ ባለስልጣን ዶኩመንቱን ለመፈርም ስልጣን እንዳለው እና
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዶኩመንቱ ላይ የተመታው ማህተም እውነተኛነትን ያረጋግጣል፤ ለምሳሌ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (notary public) ማህተም ያለበት
- ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) የዶኩመንቱን ጽሁፍ ወይም ይዘት ሃቀኛነትን አያረጋግጥም።

**ጥያቄ: ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) ለምን ያስፈልገኛል?**
መልስ፡ ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) የሚያስፈልጎት፤ ሊጠቀምበት የሚፈልገው አገር እንዲህ ዓይነቱ የማረጋገጫ ወረቀት ያስፈልገኛል ብሎ ከጠየቀ ነው። ዶኩመንቶን ማግኘት የሚፈልገው አገር፤ ምን እንደሚያስፈልገው መጀመርያ እርሶ ራስዎ ያረጋግጡ።

**ጥያቄ: ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) እንዴት ነው የሚሰጠው ?**

መልስ፡ ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille)፤ በዶኩመንትዎ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚመታ ቀለሙ ነጭና ጥቁር የሆነ የምስክር ወረቀት ነው።

ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille)፣ በበለጠ ደህንነቱ እንዲጠበቅ ተጨማሪ የደህንነት ጥበቃ ይደረግለታል። ይህም የምስክር ወረቀቱ በመስርያ ቤታችን መቼ እንደተሰጠ በዌብሳይታችን ውስጥ በልዩ ዘዴ የሚያመለክት ተጨምሮበታል። እያንዳንዱ የምስክር ወረቀት፤ ልዩ የመዝገብ ቁጥርና የምስክር ወረቀቱ መቼ እንደተሰጠ የሚያመለክት ቀን ያለበት ነው። ግንቦት (May) 15 ቀን 2018 ወይም ከዛ በኋላ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ሃቀኛነትን ለማረጋገጥ ከፈለጉ በኦንላይን ወደ apostille.sos.state.mn.us.ይግቡና ያጣሩ።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ሃቀኛነትን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (Apostille) ወይም የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (Notary) ይሰጣልን?**

መልስ: ከግንቦት (May) 15 ቀን 2018 ጀምሮ፤ የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር( Minnesota Secretary of State) ፤ በውጭ አገሮች ጥቅም ላይ የሚውል የዶኩመንቶችን ነጠላ ማረጋገጫ ይሰጣል። ዶኩመንቱ የሚላክበት አገር ያም ይሁን ይህ፤ ከአገር ውጭ በሚገኝ አገር ጥቅም የሚውል የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የማረጋገጫ ወረቀት** (Notary) **አገልግሎት ይሰጣልን?**

**መልስ:** አይሰጥም። የማረጋገጫ አገልግሎት ካስፈለገ፤ ጥያቄዎን ወደ ሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ከማቅረቦ በፊት ዶኩመንቶ በመጀመርያ ሃቀኛነትን በሚያረጋግጥ ባለስልጣን (Notary) ማስመስከር አለቦት።

**ጥያቄ: የሃቀኛነት ማረጋገጫ ወረቀት ይሰጠኝ ብዬ ያቀረብኩት ጥያቄ አስቸኳይ ነው። እኔ ግን በአካል መምጣት አልችልም። ያሉኝ አማራጮች ምንድናቸው?**

መልስ: ዶኩመንቶች መቼ እንደሚታዩ የሚወሰነው እንደየአመጣጣቸው ነው።

የሚፈልጉት የሃቀኛነት ማረጋገጫ ወረቀት አስቸኳይ ከሆነና እርሶም ሆኑ የወከሉት ሰው ወደ መስርያ ቤታችን በአካል ለመገኘት የማትችሉ ከሆነ፤ ዶኩመንቶችዎን በአንድ ለሊት ሊያደርሱ በሚችሉ በፌዴክስ (FedEx)፣ ዩ-ፒ-ኤስ (UPS)፣ ዩ-ኤስ-ፒ-ኤስ (USPS) ወይም ዲ-ኤች-ኤል ( DHL) መላክ ይፈልጉ ይሆናል።ዶኩመንቶችዎን ወደ እርሶ ዘንድ እንዲመለስሎት ደግሞ አስቀድሞ የቴምብሩ ዋጋ የተከፈለበትና በአንድ ሌሊት የሚደርስ ምልክት ያለበት ፖስታ አብረው ይላኩ።

*እባክዎን እዚህ ላይ መረዳት ያለቦት ይህ የዶኩመንቶችዎን የማጣራት ግዜ ይቀንሳል ማለት እንዳልሆነና የሚያፋጥነው ነገር ካለ፤ እርሶ አንዴ የተጠናውን ዶኩመንቶችዎን የሚያገኙበትን ግዜን ብቻ መሆኑን ነው።

**ጥያቄ: የዶኩመንት ሃቀኛነት የሚያረጋግጥ ወረቀት እንዲሰጠኝ ያቀረብኩት ጥያቄ ምንም አስቸኳይ ቢሆንም፤ ቀጠሮ ለማግኘት አልቻልኩም። ያሉኝ ምርጫዎች ምንድናቸው?**

መልስ፡ አስቸኳይ ጥያቄዎን በኢሜል ወደ apostille.oss@state.mn.us ይላኩ፡ ከመገናኛው ጋር ለመገናኘት ኮንትሮል+ ይጫኑ

## <u>በአካል የሚደረጉ ሃቀኛነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ቀጠሮዎች</u>

**ጥያቄ፡ ካለቀጠሮ ወደ መስርያ ቤታችሁ መጥቶ ጉዳይ ማስፈጸም ይቻላልን (walk-ins)?**

**መልስ:** አይቻልም። ይህንን **here** በመጫን ወይም በስልክ ቁጥር 651-296-2803 የውስጥ መስመር 2 ወደ ጽህፈት ቤታችን በመደወል ቀጠሮ ይውሰዱ።

ምን ዓይነት ቀጠሮችን እንደምንሰጥ የሚያመለክት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እዚህ ላይ **here** ይጫኑ

**ጥያቄ: የህዝብ መጸዳጃ ቤት አላችሁን ?**
**መልስ:** የለንም። መስርያ ቤታችን የሚገኘው በፊርስት ናሽናል ባንክ ህንጻ (First National Bank Building) ውስጥ ነው። ይህ ህንጻም የህዝብ መጸዳጃ ቤት የለውም።

**ጥያቄ: የሃቀኛነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው በአካል መጥቶ መጠየቅ የሚችል ማነው ?**
**መልስ:** ማንኛውም ግለሰብ የሃቀኛነት የምስክር ወረቀት (apostille) እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል። ጠያቂው የግዴታ በመጠየቂያው ፎርም ላይ ያለ ሰው ወይም በሚቀርቡት ዶኩመንቶች ውስጥ ያለ ሰው መሆን የለበትም።

**ጥያቄ: እንዴት ነው ቀጥሮ መውሰድ የምችለው?**
**መልስ:** ቀጠሮ ለማግኘት እዚህ **here** ላይ ይጫኑ ወይም በስልክ ቁጥር at 651-296-2803 የውስጥ መስመር 2 ወደ መስርያ ቤታችን ይደውሉ።

ቀጠሮን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እዚህ **here** ላይ ይጫኑ።

**ጥያቄ: ለሚመጣው ወር ቀጠሮ ማድረግ ከፈለኩ እንዴት ነው ቀጠሮ መያዝ የምችለው?**
**መልስ:** ቀጠሮዎች አስራ አራት ቀናት ቀደም ብለው ነው ሊደረጉ የሚችሉት።

**ጥያቄ: ከ10 በላይ ዶኩመንቶች አሉኝ፤ እንዴት ነው ቀጠሮ ልይዝ የምችለው?**
**መልስ:** ከ10 በላይ ዶኩመንቶች ካሎት፤ ወደ **apostille.oss@state.mn.us** በመጻፍ ልዩ ዝግጅት እንዲያደርግሎ ከመስርያ ቤታችን ጋር ተገናኙ።

**ጥያቄ: ያደረኩትን ቀጠሮ እንዴት ነው መሰረዝ የምችለው ?**
**መልስ:** የወሰዱትን ቀጠሮ መሰረዝ ወይም ቀጠሮውን ለሌላ ግዜ ማስተላለፍ የሚችሉት ገና ቀጥሮ ሲወስዱ "ቀጠሮዎ ተረጋግጧል"ወይም 'Confirmed booking for' ተብሎ ከተላከሎት ኢሚል ሊደረግ ይችላል።

ይህንን የተላከሎትን የማረጋገጫ ኢሜል ሊያገኙት ካልቻሉ ወደ **apostille.oss@state.mn.us** በመጻፍ ከእኛ ጋር ይገናኙ።

**ጥያቄ: የመኪና ማቆምያ አላችሁን ?**
**መልስ:** የመኪና ማቆምያን በተመለከተ ያሎት አማራጮች ከወደታች ተዘርዝረዋል፡

- መወጣጭያ(Ramp): የፊርስት ናሽናል ባንክ ህንጻ (First National Bank Building) የመኪና ማቆምያ መግብያው በአምስተኛው ጎዳና በስተ ምስራቅ (Fifth Street East) በኩል ነው። ማቆምያው ገንዘብ ይከፈልበታል። መኪናዎን በመጀመርያ ፎቅ ላይ ያቁሙና ወደ ላይኛው ፎቅ ለመውጣት ኤሊቫተር ይውሰዱ። ከኤሊቬተሩ ሲወጡ መስርያ ቤታችን ከዛ ፊት ለፊት ይገኛል።
- የጥርግያ መንገድ መኪና ማቆምያ፡ በሚኖሶታ ጎዳና (Minnesota St.) የሚከፈልበት የመኪና ማቆምያ የክፍያ መሳርያ/ሜትር አለ።

- ቀለል ያለ የባቡር መንገድ፡ ህንጻው ከባቡር ጣብያው አረንጓዴ መስመር እስከ ሴንትራል (Green Line – Central) ማቆምያ መስመር አንድ ብሎክ ብቻ ነው የሚርቀው።
- አውቶቡስ: ህንጻው ከአውቶቡስ ማቆምያ 2611 አንድ ብሎክ የራቀ ነው-የአውቶቡስ ማቆምያውም በ ሚኖሶታ ጎዳናና 4ኛው መንገድ (Minnesota St & 4th St.) ላይ ይገኛል።

## <u>በፖስታ የተላከ የሃቀኛነት ማረጋገጫ (Apostille) የምስክር ወረቀት</u>

**ጥያቄ: ዶኩመንቶቼን በፖስታ ነው የላኩት። ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ እንዴት ነው ማጣራት የምችለው?**
መልስ፡ ወደ apostille.oss@state.mn.us በመጻፍ ወይም በስልክ ቁጥር 651-296-2803 የውስጥ መስመር 2 ወደ መስርያ ቤታችን በመደወል ሊያውቁ ይችላሉ።

ዶኩመንቶቹ የተላኩት በቼክ ወይም በገንዘብ ትእዛዝ (money order) ተሸኝተው ከሆነ የቼኩንና የገንዘብ ትእዛዙን ቁጥር ይስጡን።

**ጥያቄ: ዶኩመንቶቼን የሄግ ስምምነት (Hague Convention ) በመባል የሚታወቀው ድርጅት አባል ወደ አልሆነ አገር ነው የምልከው፣ እንዴት ብሎ ነው ሃቀኛነቱ ሊረጋገጥ የሚችለው?**
መልስ: የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የሄግ ስምምነት( **Hague Convention** )) አባል ይሁንም አይሁን፤ ከአሜሪካን አገር ውጪ ባለ አገር ጥቅም ላይ የሚውል አንድ ነጠላ የሃቀኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይልካል።

እርግጠኛ ካልሆኑ፤ ዶኩመንቱን ለመላክ ከሚፈልጉት አገር ኤምባሲ ወይም ቆንስል ጋር ተገናኝተው ስለዚሁ ጉዳይ ስላሎት አማራጮች ተነጋገሩ።

## <u>የሚኖሶታ ወሳኝ ኩነት መዝገቦች</u>

**ጥያቄ: የልደቴ የምስክር ወረቀት እንዴት ነው ሃቀኛነቱ እንዲረጋገጥልኝ የማደርገው ?**
**መልስ:** የሚኖሶታ የልደት የምስክር ወረቀት ከሆነ፤ መጀመርያ እርሶ ለመሆንዎ የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት መላክ አለቦት። የልደት የምስክር ወረቀቱ በሌላ ክፍለሃገር (state) የተሰጠ ከሆነ ደግሞ ከዛው የልደት ምስክር ወረቀቱን ከሰጦት ክፍለ ሃገር (state) የሃቀኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለቦት።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የተረጋገጠ የልደት ምስክር ወረቀት ማግኘት የምችለው ከየት ነው?**
**መልስ:** እባክዎን በሚኖሶታ የጤና ጥበቃ መምሪያ ውስጥ ከሚገኘው የአስቸኳይ ሁኔታ መዝገቦች ክፍል (**The Office of Vital Records at the Minnesota Department of Health** (የልደት የምስክር ወረቀቶች) በመጫን ይመልከቱ።

**ጥያቄ: ረጅም ቅርጽ ላለው (long-form )የልደት የምስክር ወረቀት እንዴት ነው የሃቀኛነቱን ማረጋግጫ የማገኘው ?**
**መልስ:** የሚኖሶታ ክፍለ ሃገር ረጅም ቅርጽ ያለው (long-form) የልደት የምስክር ወረቀት መስጠቱን አቁሟል። እዚህ **here** ይመልከቱ

የሚኖሶታ የጤና መምሪያ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት፣ ያልተረጋገጠ የልደት የምስክር ወረቀት እና ረጅም ቅርጽ ያለው (long-form) የልደት የምስክር ወረቀት የመመሪያ ማስታወሻ ይሰጣል።

*** አስተውሉ፡ ሶስቱ ዶኩመንቶች ወይም ሰነዶች እንደ አንድ ዶኩመንት ወይም ሰነድ ሊቀርቡ አይችሉም። የተረጋገጠው የልደት የምስክር ወረቀት ብቻውን እንደ አንድ ዶኩመንት ወይም ሰነድ መቅረብ አለበት። ገና ያልተረጋገጠው የልደት የምስክር ወረቀት እና ረጅም ቅርጽ ያለው (long-form) የልደት የምስክር ወረቀት የመመሪያ ማስታወሻ ሁለቱም በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) መጀመርያ መረጋገጥ አለባቸው፤ ከዛ በኋላ ሃቀኛነታቸው እንዲረጋገጥ ( apostille) መቅረብ ይችላሉ።

**ጥያቄ: የተረጋገጠ የሞት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የት ነው የማመለክተው ?**
**መልስ: ይህንን** በሚኖሶታ የጤና ጥበቃ መምርያ ውስጥ ያለውን የአስቸኳይ ሁኔታ መዝግቦች መስርያ ቤትን (**The Office of Vital Records at the Minnesota Department of Health**)።

**ጥያቄ: የሞት የምስክር ወረቀትን ሃቀኛነት ለማስመስከር የት ነው የማመለክተው ?**
**መልስ:** የሞት የምስክር ወረቀቱ ከሚኖሶታ የተገኘ ከሆነ፤ መጀመርያ በህዝብ ማመሳከርያ ባለስልጣን (Notary Public) ማስመስከር አለቦት፤ ከዛ በኋላ ወደ እኛ ይልኩታል፤ ከዛ በኋላ ነው የሃቀኛነት ማረጋገጫ የሚሰጡት። የሞት የምስክር ወረቀቱ የተገኘው ከሌላ ክፍል ሃገር ከሆነ ደግሞ ከዛ የምስክር ወረቀቱን ከሰጥቶት ክፍለ ሃገር ጋር መነጋገር አለቦት።

**ጥያቄ: የጋብቻ የምስክር ወረቀት እንዴት ነው ሃቅነቱ እንዲረጋገጥልኝ ማድረግ የምችለው?**
**መልስ:** በህዝብ ማመሳከርያ/ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) የተመሰከረለት የሚኖሶታ የጋብቻ የምስክር ወረቀት መላክ አለቦት። የተመስከረለት የጋብቻ የምስክር ወረቀት ቅጂ ከሌሎት፤ ከዛው የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ካውንቲ ወይም አውራጃ ጋር ተነጋገረው ቅጂ ማግኘት አለቦት።

እባክዎን ወደዚህ ወደ ተጻፈው የጋብቻ የምስክር ወረቀት **Marriage Certificates**።

**ጥያቄ: የመታሰብያ (keepsake souvenir) የሚኖሶታ የጋብቻ የምስክር ወረቀት አለኝ። ይሄ ሃቀኝ መሆኑ እንዲረጋገጥልኝ ወደ እናንተ ጋ ልላከውን?**

**መልስ:** የለም፣ አትላኩት። የሃቀኛነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በህዝብ ማመሳከርያ/ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public)መጀመርያ የምስክር ወረቀቱ ሲረጋገጥ ነው። ስለዚህ እርሶ በህዝብ ማመሳከርያ/ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ነው መላክ ያለቦት። በህዝብ ማመሳከርያ ባለስልጣን (Notary Public) የተመሰከረለት የጋብቻ የምስክር ወረቀት ቅጂ ከሌሎት፤ ከዛው የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ካውንቲ ወይም አውራጃ ጋር ተነጋገረው ቅጂ ማግኘት አለቦት።

እባክዎን ወደዚህ ወደ ተጻፈው የጋብቻ የምስክር ወረቀት **Marriage Certificates**።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ መምሪያ የምስክር ወረቀቶችን (ለምሳሌ የልደት/የሞት/የጋብቻ የምስክር ወረቀቶች) ለመተርጎም የትርጉም አገልግሎት ይሰጣልን?**
**መልስ:** አይሰጥም። ትርጉም ካስፈለገ፤ ከመስሪያ ቤታችን ውጪ ሌሎች የትርጉም አገልግሎት እንዳሉ ራስዎ ፈልገው ማስተርጎም አለቦት።

**ጥያቄ: የተተረጎሙት የልደት/የሞት/ የጋብቻ የምስክር ወረቀቶቼን እንዴት ነው ሃቀኛነታቸው እንዲረጋገጥልኝ ማድረግ የምችለው?**
**መልስ:** የተተረጎሙት ዶኩመንቶች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (notary public) መጀመርያ በደንብ መረጋገጥ አለባቸው። መስርያ ቤታችን የሃቀኛነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ፤ ዶኩመንቱ የሃቀኛ ዶኩመንት ትርጉም መሆኑን የተገለጸበት ጽሁፍ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፈ መሆን አለበት። ሌላው የተቀረው የዶኩመንቱ ክፍል በማንኛውም ሌላ ቋንቋ ሊሆን ይችላል።

አስተውሉ: የተተረጎመው ዶኩመንት በተናጠል ነው ሃቀኛነቱ የሚወሰነው። ለምሳሌ የተረጋገጠ የሚኖሶታ የልደት የምስክር ወረቀት በደንብ ከተረጋገጠ፤ የልደት ምስክር ወረቀት ትርጉም ወይም ቅጂ ጋር እንደ አንድ ዶኩመንት ሊቀርቡ አይችሉም። ሁለቱ ዶኩመንቶች እንደ ሁለት የተለያዩ ዶኩመንቶች ነው የሚቀርቡት። እያንዳንዱ ዶኩመንትም የራሱን የሃቀኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኛል።

**ጥያቄ: ያላገባሁ መሆኔን የሚገልጽ ደብዳቤ ከየት ነው የማገኘው? ያላገባሁ መሆኔን የሚገልጽ ደብዳቤን እንዴት ነው ሃቀኛነቱን ማረጋገጥ የምችለው?**
**መልስ:** ይህ ያላገቡ መሆኖን የሚገልጸው ደብዳቤ፤ አብዛኛውን ግዜ ጋብቻ መፈጸሙን የማያሳይ የምስክር ወረቀት (Certificate of No Record of Marriage) ተብሎም ይጠራል። በአጠቃላይ ይህ የምስክር ወረቀት ከካዊንቲዎ ወይም ከአውራጃዎ ሊገኝ ይችላል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ኦንላይን ገብተው (Single Status Affidavits) ተብሎ እንደ ምሳሌ የቀረበውን ፎርም በመሙላት ቅጇውን በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (MN Notary Public) ሊያረጋግጡ ይችላሉ።

*እባክዎን አስተውሉ፡ ይህንን ያላገቡ መሆንዎን የሚገልጽ ደብዳቤ፤ በተለይ ማግኘት የሚፈልጉት ከሄነፒን ካውንቲ (Hennepin County) ከሆነ፤ የሄነፒን ካውንቲ (Hennepin County) የእንደዚህ ዓይነት ደብዳቤዎችን ሃቀኛነት የማረጋገጥ አገልግሎት እንደማይሰጥ አስታውቋል። ስለዚህ ሃቀኛነቱን የማረጋገጥ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ (a Minnesota Notary Public) መረጋገጥ አለበት።

## <u>የድህረ-ታሪክ ምርመራ/ የወንጀል ታሪክ መዝገብ</u>

**ጥያቄ: በሚኖሶታ የተደረገ የድህረ ታሪክ ምርመራ/የወንጀል ታሪክ መዝገብ ሃቀኛነት እንዲጣራ እንዴት ነው ማድረግ የምችለው?**
**መልስ:** ይህንን ለማድረግ ከወንጀል ስጋት ቢሮ (Bureau of Criminal Apprehension) ደብዳቤ ማግኘት አለቦት። ስለዚህ የድህረ ታሪክ ምርመራ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፤የወንጀል ስጋት ቢሮ ዌብሳይት **[Bureau of Criminal Apprehension website]** በማድረግ ገብተው ይጎብኙ።

**ጥያቄ: የአሜሪካ መንግስት የምርመራ ቢሮ- ኤፍ-ቢ-አይ (FBI) ስለእኔ ያደረገውን የድህረ-ታሪክ ጥናት እንዴት ነው ሃቀኛነቱ እንዲረጋገጥ የማስደርገው?**
**መልስ:** የአሜሪካ ፌደራል የምርመራ ቢሮ- (FBI)ያደረገው የድህረ-ታሪክ ጥናት በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ወደሚገኘው የአሜሪካ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው መላክ ያለበት። መስርያ ቤታችን በመንግስት የተደረገ የመንግስት ድህረ-ታሪክ ምርመራን ሃቀኛነት የማጣራት ስልጣን የለውም። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **[US Department of State]**

## <u>የሚኖሶታ የትምህርት ቤት ዶኩመንቶች</u>

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት መዝገቤ በህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public)መረጋገጥ አለበትን ?**
**መልስ:** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት መዝገብ በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) መረጋገጥ አለበት።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማዬ በህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public)መረጋገጥ አለበትን ?**

**መልስ:** ዲፕሎማዎች (ኦሪጂናልም ሆኑ ቅጂ) በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) በደንብ መረጋገጥ አለባቸው።

አስተውሉ: የሚመለከተው አገር የሚያስፈልገው ዲፕሎማ ኦሪጂናል ነው ወይስ ቅጂውን ይቀበላል የሚለውን ጥያቄ በማቅረብ በቅድምያ ያረጋግጡ።

**ጥያቄ: ጥያቄ: የሚኖሶታ ኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ የትምህርት መዝገቤ ሃቀኛነቱ እንዲረጋገጥልኝ ማድረግ ያስፈልገኛልን ?**
**መልስ:** የኮሌጅ/የዩኒቨርሲቲ የትምህርት መዝገቦች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public ) መረጋገጥ አለባቸው።

**ጥያቄ: የሚኖሶታ ኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ ዲፕሎማዬ ሃቀኛነቱ እንዲረጋገጥ ማድረግ ያስፈልገኛልን ?**
**መልስ:** የኮሌጅ/የዩኒቨርሲቲ ዲፕሎማዎች (ኦሪጂናልም ሆነ ቅጂው) በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public ) መረጋገጥ አለባቸው።

አስተውሉ: የሚመለከተው አገር የሚያስፈልገው ዲፕሎማ ኦሪጂናል ነው ወይስ ቅጂውን ይቀበላል የሚለውን ጥያቄ በማቅረብ ያረጋግጡ።

**ጥያቄ: ከሌላ ክፍለሃገር ያገኘሁትን የትምህርት መዝገብ እውነተኛ መሆኑ እንዲረጋገጥልኝ እንዴት ነው ማድረግ ያለብኝ?**
**መልስ:** ይህንን ለማድረግ ከዛ የትምህርት ዶኩመንት/መዝገብ ካገኙበት ክፍለ ሃገር ጋር ነው መነጋገር ያለቦት።

<u>*የመንጃ ፈቃድ/ የመታወቅያ ወረቀት*</u>

**ጥያቄ: የመንጃ ፈቃዴ/ የመታወቅያ ወረቀቴ ሃቀኛ መሆናቸውን እንዴት ነው እንዲረጋገጥልኝ የማደርገው?**
**መልስ:** የመንጃ ፈቃዶንና የመታወቅያ ወረቀቶን ቅጂ ወደኛ ጋ ከመላክዎ በፊት በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public ) ሃቀኛውና ትክክሉ ግልባጭ ወይም ቅጂ መሆኑን ማረጋገጥ አለቦት። እባክዎን ዋናውን የመንጃ ፈቃዶንና የመታወቅያ ወረቀቶን ወደ እኛ ጋ አይላኩ።

**ጥያቄ: ፓስፖርቴ ሃቀኛ መሆኑን እንዲረጋገጥልኝ እንዴት ነው የማደርገው?**
**መልስ:** የፓስፖርትዎን ቅጂ ወደኛ ጋ ከመላክዎ በፊት በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public ) ሃቀኛውና ትክክሉ የፓስፖርትዎ ግልባጭ ወይም ቅጂ መሆኑን ማረጋገጥ አለቦት። እባክዎን ዋናውን(ኦሪጂናል) ፓስፖርትዎን ወደ እኛ ጋ አይላኩ።

<u>በህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን **(Notary Public )** የተረጋገጡ ዶኩመንቶች</u>

**ጥያቄ: እንዴት ነው የግል ዶኩመንቶቼን ሃቀኛነት ለማረጋገጥ የምችለው (ለምሳሌ የውክልና ወረቀት፣ በመሃላ የተሰጡ መግለጫዎች፣ ፍቃዶች..ወዘተ)?**
**መልስ:** የግል ዶኩመንቶች በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) እንዲረጋገጡ ማድረግ አለቦት።

**ጥያቄ: ዶኩመንቴ በትክክልና በተገቢው መንገድ እንደተረጋገጠ እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?**
**መልስ:** በህግ ቁጥር MS 358.65 መሰረት፤ የሚኖሶታ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) ለሆነ ዶኩመንት ማረጋገጫ ሲሰጥ የሚከተሉትን መዘርዘር አለበት፡

- ያለው ስልጣን (ለምሳሌ የሚኖስታ ክፍለሃገር፤ የራምሲ አውራጃ... )
- የእውቅና መግለጫ
- የስራው ዓይነት (ለምሳሌ -Notary Public)
- የተረጋገጠበት ቀን
- በእጅ ወይም በብዕር የተፈረመ ኦሪጂናል ፊርማ
- የባለስልጣን ማህተም

**ለተወሰኑ ምሳሌዎች የሚሆኑ የዶኩመንት ዓይነቶች Types of Documents ገጽ**

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጪ በሌላ ቋንቋ ለተጻፈ ዶኩመንት ወይም ሰነድ የሃቀኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላልን?**
**መልስ:** አዎን። ዶኩመንቱ የተሰጠው ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተጻፈው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ከሆነ፤ የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የዶኩመንቱን ሃቀኛነት የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት መስጠት ይችላል። ቀሪው ዶኩመንት በማንኛውም ቋንቋ ሊሆን ይችላል።

**ጥያቄ: መስርያ ቤትዎ የእኔ ዶኩመንት የእኔ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላልን?**
**መልስ:** የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት አይሰጥም። በሚኖሶታ ያሉትን የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Notary Public) ጽህፈት ቤቶችን ለመፈለግ እዚህ **here** ይጫኑ

**ጥያቄ: ከሌላ ቦታ ሆኖ ወይም በኤሌክትሪካዊ መንገድ የሚደረግ ማረጋገጫ ይቀበላሉን?**
**መልስ:** አንቀበልም። የሚኖሶታ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) የተረጋገጠና በኤሌክትሪካዊ መንገድ የተፈረመ ዶኩመንት፤ እንደ የኦሪጂናሉ ዶኩመንት ቅጂ ስለሚመለከተውና ቅጂ የህዝብ ዶኩመንት ስላልሆነ የሃቀኛነት ማረጋገጫ ከመደረጉ በፊት፤ ዶኩመንቱ በሚኖሶታ የህዝብ ማረጋገጫ ባለስልጣን (Minnesota Notary Public) መረጋገጥ አለበት።

## የሚኖሶታ የንግድ ቦታዎች መዛግብት

**ጥያቄ: የሚኖሶታ የንግድ ስራ ዶኩመንቶቼን እንዴት ነው ሃቀኛነታቸውን ማረጋገጥ የሚቻለው?**
**መልስ:** በሚኖሶታ ውስጥ የለው የንግድ ስራ በመስርያ ቤታችን የተመዘገበ ከሆነ፤ የተመሰከረለትን ቅጂ ለማግኘት ጥያቄ ያቅርቡ። ከታች ሁለት አማራጮች ሰፍረዋል።

- አማራጭ 1: ኦንላይን ይግቡና የተረጋገጠውን ቅጂ በቀጥታ ያግኙ። መመሪዎችን እዚህ **here** የፋይሎች ቅጂ እንዴት ማዘዝ እንደሚቻል

እነኚህ የተረጋገጡ ቅጂዎች በኢሜል ይላክልዎታል። አንዴ ካገኟቸው በኋላ የሁሉንም የመዝገብ የምስክር ወረቀት (Certification of Record) ገጾችን አትመው፤ ከማረጋገጫ ጥያቄ ፎርምና ከተገቢው ክፍያ ጋር ወደ እኛ ይላኩ **Authentication Request Form**።

- አማራጭ 2: ይህንን የንግድ ስራ የጥያቄ ፎርምና የማረጋገጫ ጥያቄ ፎርም (**Business Copy Request Form** and **Authentication Request Form**) ሞልተው ያጠንቅቁ። ወደዚህም የሚገቡት፤ የስራ ቅጂ/የምስክር ወረቀት ወደሚለው ይገባሉ፤ ከዛም ፎርሞቹን ተገቢውን ቅጂና ተገቢውን የማረጋገጫ ክፍያን አስታከው በፖስታ ወደ እኛ መስርያ ቤት ይላኩ።

**ጥያቄ: አሁንም በስራ ላይ ጥሩ እንዳለሁና መልካም ስም እንዳለኝ የሚገልጽ የምስክር ወረቀቴን እንዴት ነው ሃቀኛነቱ እንዲረጋገጥልኝ (apostille) የማደረገው?**
**መልስ:** በመስርያ ቤታችን የተመዘገበ፤ በሚኖሶታ አሁንም በስራ ላይ ያለ ከሆነና ጥሩ አቋም ወይም መልካም ስም ካለው፤ ከታች ሁለት አማራጮች ተመዝግበዋል፡

- አማራጭ 1: ጥሩ ስምና በስራ ላይ ያለ የሚል የንግድ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በኦንላይን በቀጥታ ይዘዙ። መመርያዎቹ እዚህ **here** ገብተው።

ይህ የምስክር ወረቀት በኢሜል ይላክሎታል። ሲደርሶት አትመው በማውጣት ወደ እኛ መስርያ ቤት ከማረጋገጫ ጥያቄ ፎርምና (**Authentication Request Form)** ከተገቢው ክፍያ ጋር ይላኩ።

አማራጭ 2: የንግድ ቅጂ ጥያቄ ፎርም (**Business Copy Request Form)** እና የሃቀኛነት ማረጋገጫ ጥያቄ ፎርም (**Authentication Request Form**) ይሙሉና ተገቢ ከሆነው የምስክር ወረቀትና የማረጋገጫ ክፍያ ጋር ወደ መስርያ ቤታችን ይላኩ።